የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 29
ADDIS ABABA 28th May, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፩/፪ሺ፬ ዓ.ም

ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማስፋፊያ ሁለተኛ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከአለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ …… **ገጽ ፮ሺ፫፻፴**

CONTENTS

**Proclamation No.741/2012**

International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Financing Rural Financial Intermediation Program II Ratification Proclamation. ... Page 6330

## አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፩/፪ሺ፬

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማስፋፊያ ሁለተኛ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ.ዲ.አር. ፴፩ ሚሊዮን ፫፻ሺ (ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር.) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፩ በሮም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፴ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ማስፋፊያ ሁለተኛ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ ከአለም ዓቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ ጋር የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፵፩/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 741/2012.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of thirty one million three hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 31,300,000) for financing Rural Financial Intermediation Program II was signed in Rome on the 21st day of December 2011;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 8th day of May 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-article (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Fund for Agricultural Development Loan Agreement for Financing Rural Financial Intermediation Program II Ratification Proclamation No.741/2012".

## ፪. <u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የግብርና ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፩ በሮም የተፈረመው ቁጥር I-844-ET የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፴፩ ሚሊዮን ፫፻ሺ (ሰላሳ አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፳ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Loan Agreement No.I-844-ET signed in Rome on the 21st day of December 2011, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Fund for Agricultural Development is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Development</u>

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of thirty one million three hundred thousand Special Drawing Rights (SDR 31,300,000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 28th day of May, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**